የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ
TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: czanareg@hotmail.com

# በጥላቻ ማፍረስ እንጂ መገንባት አይቻልም ።

ዛሬ አገራችን የተዘፈቀችበት ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ስናጤን እንኳን በቅራኔና በጥላቻ እርስ በርሳችን እየተጠላለፍን፣ ባንድነት ተያይዘን ተጉዘንም በቀላሉ የሚቀረፍ እንዳልሆነ ጠንቅቀን ልናውቀው የሚገባ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊያን ኃይሎችና አገር ወዳዶች በመካሄድ ላይ ያለው ህዝባዊ ትግል መንገዱን ሳይስት የታለመለት ግብ እንዲደርስ ያላሰለሰ ትግል የሚካሂዱት ይህንን እውነታ በሚገባ በመረዳታቸው መሆኑንም እናውቃለን። ይሁን እንጂ ይህንን ውስብስብ ችግር ቀርፎ የሚፈለገውን ግብ ለመድረስ ገና ብዙ ሥራ መሰራት እንዳለበት የሚያጠያይቅ አይደለም። የኢህአዴግን መሠሪ ከፋፋይ ስልት የሚከተሉ ራስ ወዳድ የጥላቻ ኃይሎች ህዝብን ከህዝብ ጋር ለማባላት ከየአቅጣጫው የሚያሰራጩት ፕሮፓጋንዳ ስፋትና ጥልቀት ከምን ጊዜም በላይ እየጨመረ ነው። ይህ ሂደት በዚህ ከቀጠለ ደግሞ በህዝቦች መካከል አለመተማመንን ይፈጠራል። ይህ አለመተማመንም በተራው መበታተን ያስከትላል።

ዛሬ ላገራችን ህልውና አደጋ ሆነዋል የምንላቸው የሁለቱ ኃይሎች ገፀ-ባሕሪያት ከኢህአዴግ ጀምረን ከዚህ ቀጥለን በየተራ ለመግለጽ እንሞክራለን።

አምባገነኑ የኢህአዴግ ቡድን የመከፋፈል እንጂ  በጋራ የጋራ አገርን የመገንባት ብሔራዊ አጀንዳ እንደሌለው ለኢትዮጵያ ህዝቦች መነገር የሚገባው አዲስ መርዶ አይሆንም ። ይህንን በሚገባ የሚያውቁትና የተረዱት ከመሆኑም በላይ የዚህ አገር አጥፊ ቡድን ተግባርን አስመልክተን ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ዘግበናል፣ የቡድኑ ተግባር ራሱም ይህንን ሓቅ ይመሰክራል። ይህ ቡድን አገር የከዳ ኃይል መሆኑን ህዝቦቻችን ጠንቅቀው አውቀውታል። የህዝብ ውክልና ሳይኖረው ኤርትራን ማስገንጠል፣ አገራችንን የባሕር በር አልባ አድርጎ ለማስቀረት ባለቤት ነኝ ከሚለው ሻዓቢያ በላይ የኤርትራ ጠበቃ ሆኖ በመከራከር የኢትዮጵያ ህዝቦች ጥቅምና መብትን ማስነጠቅ፣ የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት የሻዓቢያ መፈንጫ እንዲሆን በፍላጎት መፍቀድ፣ የኢትዮ-ኤርትራ የ"ድንበር" ጦርነት አወጋገን፣ የአልጀርስ ስምምነት፣.....ወዘተ. ከምናውቃቸው ብዙ ክህደቶች ውስጥ በትንሹ መጥቀሱ ይህ ቡድን ለኢትዮጵያ የያዘው አጀንዳ ምን እንደሆነ በቀላሉ ለመረዳት ያስችለናል። ስለሆነም ከዚህ አምባገነን ቡድን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ህዝቦች የሚበጅ ቁምነገር እንዲፈልቅ መጠበቅ አይቻልም። ይህ ቡድን ተጠሪነቱ ድጎማና ብድር በመስጠት የሥልጣን ዕድሜውን እንዲያራዝም ለሚረዱት የውጭ ኃይሎች እንጂ ለኢትዮጵያ ህዝቦች እንዳልሆነ ከተገነዘብን ውለን አድረናል። በብሔራዊ ማንነታችን የምናፍርበት ቡድን እንጂ የምንመካበትና የምንኮራበት ሆኖ ለመውጣት የታደለ አይደለም። የውጭ አሳዳሪዎቹን ለማስደሰት የማይጓዘው ርቀትና አሳልፎ ሊሰጠው የማይቻለው ብሔራዊ ጥቅምም አይኖርም። ቀድሞ አልጀርስ ላይ በገባው ውል፣ ቀጥሎም ሔግ ላይ በሰጠው ምስክርነት፣ ሉዓላዊ ግዛታችንን አሳልፎ ከመስጠቱም በላይ ሔግ ላይ ብይን በተሰጠበት ዕለት ሉዓላዊ ግዛቶቻችንን መነጠቃችን እያወቀ አሸነፍን ብሎ ያለ ምንም ሓፍረት ህዝቡን ለጭፈራ በመገናኛ ብዙኃን እስከመጋበዝ የደረሰ ለሎሌነት ራሱን ያዘጋጀ ቡድን መሆኑ ይታወቃል። የኢትዮጵያ ህዝቦች ግን ቀድመውት ነቅተው ጉዳዩን ሲከታተሉ በመቆየታቸው ቡድኑ እንደቋመጠው ለጭፈራና እልልታ አልወጡም። ሽንፈቱን አታልሎ ለማለፍ ቢሞክርም ህዝቦቻችን እውነቱን ለማግኘት ጊዜ አልወሰደባቸውም። ቡድኑ ለኢትዮጵያ ያለው ታማኝነት ቀድሞም በጥርጣሬ ዓይን ሲታይ የቆየ ቢሆንም በለመደበት ማጭበርበር እንዲህ በቀላሉ ሊያሞኘን መሞከሩ ግን ክህደቱን ብቻ ሳይሆን ጅልነቱንም ለመታዘብ አስችሎናል።

የዚህ ከሀዲ ቡድን ሌላው ልዩነት የታየው፤ ከግንቦቱ ምርጫ በፊትም ሆነ በኋላ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስለ አገራችን ጉዳይ እንመካከር በማለት ተደጋጋሚ ጥሪ ቢያቀርቡለትና ሽማግሌ ቢልኩበትም፤ የተለያዩ አመለካከቶችን ከሚወክሉ ኢትዮጵያዊያን ጋር በጠርጴዛ ዙርያ ተቀምጦ ለመወያየት ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘቱ ነው። የአሳዳሪዎቹን ፍላጎት በማሟላት ልዩነቱን ለማሳየት ሲል ግን ሉዓላዊ ግዛታችንን አስረክቦ ከሻዓቢያ ጋር ለመሸማገል ደጅ በመጥናት ላይ ይገኛል። በዚህ ተግባሩም ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ነው ብሎ ራሱም ቢሆን እንደማያምን በግልጽ አስመስክሯል።

የዚህ ከሀዲ ቡድኑ ወንጀል በዚህ አያበቃም። አገሪቱንና ህዝቦቿን እጅጉን የሚጎዳና፤ ህልውናችንን የሚፈታተን በህዝቦች መካከል የሚያነሳሳውና የሚያስፋፋው የሰላ የውስጥ ቅራኔ፤ ከዕለት ወደ ዕለት የከፋ መልክ እንዲይዝ በማበረታታቱም ጭምር ነው። ይህ ቡድን አብሮ ተቻችሎ የመኖር ባህላችንንና ታሪካችንን በመሸርሸር እየለያየን ይገኛል። ጥላቻ በማስፋፋት ህዝብን አራርቆ በከፋፍለህ ግዛ ዘይቤ እየተጠቀመ የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዝም እየሠራ መሆኑም በገሀድ እየታየ ነው። የብሔር ብሔረ-ሰቦች መብት አስከበርኩ እያለ ባዶ ስብከት ቢነዛም በተግባር የሚታየው ግን አንዱን ከሌላው ሲያፋጅ ነው። የጌዲዮ፤ የቴፒና መሰንጎ፤ የጋምቤላ፤ የዓፋርና ዒሳ፤......ወዘተ. ግጭቶችና የብዙ ሰው ህይወት መጥፋት የብሔር ብሔረ-ሰቦች መብት መረጋገጥን አያመለክትም። የሚያመለክተው አብሮ ተከባብሮና ተቻችሎ የመኖር ባህልና ልምድ መጥፋቱ ነው። ይህም አገዛዙ ህዝብን ከፋፍሎ ለመግዛት እንዲያመቸው የነደፈው ህዝብን ከህዝብ ጋር የማጣልት ስልት ከመሆን ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም። አገዛዙ ያሰለፋቸው አደግዳጊዎችና ጥቅም አሳዳጆችም "ውሻ በበላበት ይጮሃል" እንዲሉ በህዝቦች ላይ ያነጣጠረውን የአገዛዙ የማጣለት ሴራ የተቃወመን ሁሉ፡ ነፍጠኛ፤ ትምክህተኛ፤ ኢሠፓ፤ ኢዲዩ......ወዘተ. የሚሉና የተለያዩ ሌሎች ልጠፋዎች በመፈብረክ የስድብ ናዳ ሲያወርዱ ይደመጣሉ። ደግንቱ ጉድጓዱን በገዛ እጁ የቆፈረውን አገዛዝ ከውድቀት ለማዳን አለመቻላቸው ነው።

ከዚህም በተጨማሪ የኢህአዴግ መሪዎች ዛሬ የተቃወማቸውን ሁሉ "ኢንተርሀመዌ" ፤ ዘር ለማጥፋት የተነሳሳ ፤ መንግሥትን "ሕገ-መንግሥታዊ" ባልሆነ መንገድ ለመገልበጥ የተመኘ ወዘተ. በሚሉና በሌሎች የፈጠራ ክሶች በመወንጀል ቁም ስቅሉን እያሳዩት ይገኛሉ። በምርጫ ድምጹን ሰጥቶ በቆጠራ ድምጹን የተነጠቀን ህዝብ ድምፄ ይከበርልኝ ብሎ አብየት ማለቱ እንደ ወንጀል ተቆጥሮበት በየሄደበት በጥይት እየተቆላ ነው። በግፍ በየጫካው እየታሰረ ፤ ከቀያውና ከቤት ንብረቱ እየተነቀለ፤ ከአውሬ የማይሻሉ ካደሬዎች እያሳደዱት የሚገኘው ህዝብ ቁጥሩ ብዙ ነው። የህዝቡን ድምጽ ሲያስተጋቡ የነበሩ ጋዜጦች ተዘግቷል። ባለቤቶቹም ከኢህአዴግ ጓዳ በተፈለፈለ ወንጀል ክስ ተመሥርቶባቸው እስርቤት ተወርውረዋል። ህዝብም ድምጹን የሚያሰማበት መድረክ አጥቶ የኢህአዴግ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ እንዲሆን ተበይኖበታል። ይህ ደግሞ ማነኛውም ከቀን ወደ ቀን የሥልጣን ዕድሜው እንደ ጥላ እየሸሸው የሚሄድ አምባገነን አገዛዝ የሚፈፅመው የተለመደ የወንጀል ተግባር ነው። ስለሆነም ዛሬ የኢህአዴግ መሪዎች እየፈጸሙት የሚገኘው ወንጀል ከዚህ ተለይቶ የሚታይ አይደለም።

ሌላው እጅግ አስነዋሪ ሆኖ የምናገኘው ጉዳይ ደግሞ የኢህአዴግ ካደሬዎች፤ መገናኛ ብዙኃንና የጥቅም ተጋሪዎች የሚያሰራጩት የጥላቻ ዘመቻ ነው። የትግራይ ህዝብን ታጋች አድርጎ በመያዝ በሱ ጫንቃ የሥልጣን ዕድሜ ለማራዘም ሲባል የማይረጩት የጥላቻ መርዝ የለም። ባሁኑ ሰዓት የተለመደው መርዘኛ የጥላቻ ዘመቻቸው ያተኰረው በቅንጅት ላይ ነው። ቅንጅት የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት የተነሳ ድርጅት እንደሆነ አስመስለው ሲያቀርቡ እያየንና እየሰማን ነው። ለዚህ መርዘኛ ፕሮፓጋንዳቸውም ቀጥለን የምንገልጻቸው ጽንፈኞች የሚያራግቡት በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ መርዝን እንደ ማስረጃ ለማቅረብ እጅጉን ተጠቅመውበታል። ብዙኃኑ የትግራይ ህዝብ ደግሞ ከኢህአዴግ መገናኛ ብዙኃን ውጭ ሌላ አማራጭ የዜና ምንጭ የለውም። በህወሓት መገናኛ ብዙኃን የሚሰራጭለት ደግሞ ያው በየአከባቢያችን ሲነገር የምንሰማው የ"ቅንጅት ሊያጠፋህ መጣብህ" በመርዝ የተቀመመ ፕሮፓጋንዳ ነው። መሪዎቹ በግፍ እስር ቤት የታጕሩበት ቅንጅት ራሱን ለመከላከል ካለመቻሉም በላይ እንደ ኢህአዴግ መልእክቱን በቀላሉ ለመላው ህዝብ ለማስተላለፍ የሚችልበት መገናኛ ብዙኃን የሉትም። የአገሪቱ መገናኛ ብዙኃን ሙሉ በሙሉ ኢህአዴግ ቁጥጥር ሥር ገብቷል። በዚህም ህዝቡ ተደናግጦ ወደ ኢህአዴግ ካምፕ/ጎራ እንዲገባ ለማድረግ ካገባብ ውጭ በመሠሪነት እየተጠቀሙበት ነው።

እዚህ ላይ አንድ ግልጽ መሆን የሚገባው ጉዳይ ቢኖር ግን ዛሬ የኢህአዴግ መሪዎች ፣ ተላላኪ ካድሬዎቹና የጥቅም ተጋሪዎቹ ሊያሳምኑን እንደሚከጅሉት ቅንጅት እንደ ድርጅት የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት የተነሳ ድርጅት ነው ብለን ለመቀበል የሚያስችለን ምንም ዓይነት መረጃ የለም። ቅንጅትን እንደ ድርጅት የምንለካው አተገብረዋለሁ ብሎ ከሚታገልለት የፖለቲካ ፕሮግራሙ አንጻር ነው። ፕሮግራሙን በተግባር ለመተርጐም የሚችልበት አጋጣሚ አግኝቶ ቢሆን ኖሮ ተግባርና ቲዎሪውን አይተን ለመፍረድ በቻልን ነበር። አሁን በምናየው ግን በፕሮግራሙ ውስጥ የዘር ጥላቻን የሚያንፀባርቅ ይዘት አላየንበትም። አምባገነኑ የኢህአዴግ አገዛዝም ቢሆን አዲስ አበባ ውስጥ በቅንጅት የተጠራ ደማቅ የቅድመ ምርጫ የተቃዋሚዎች የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፍ እስከ ታየበት ጊዜ ድረስ ድርጅታዊ እውቅና ሰጥቶ በፖለቲካ መድረክ ላይ ለምረጡኝ ውድድር በመገናኛ ብዙኃን ለህዝብ እየታየ ሲከራከር "ከዘረኛ ድርጅት/ድርጅቶች" ጋር በመገናኛ ብዙኃን ለህዝብ የሚሰራጭ ክርክር አላደርግም ብሎ ሲያምጽ አላያየንም። በመሆኑም ኢህአዴግ ዛሬ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎችን በተለይ ደግሞ ቅንጅትን ዘርን ለማጥፋት በመቀስቀስና ባገር ክህደት መክሰሱ እጅጉን አሳፋሪ ሆኖ እናገኘዋለን። የክህደቱን ነገር ካነሳን ግን ባገር ክህደት የሚጠየቀው የኢህአዴግ አመራር መሆኑ አሳምረን እናውቃለን። ዘር ማጥፋት የሚለውን በሚመለከት ደግሞ የጋምቤላው የአኙዋክ ህዝብ ጭፈጨፋ በማን እንደተፈጸመ የሚታየው እነ መለስ ፍርድ ቤት ቀርበው መልስ ሲሰጡበት ይሆናል። ስለዚህም ባሁኑ ሰዓት በቅንጅትም ሆነ በሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና አመራሮች ላይ እየደረሰ ያለውን ፍርደ ገምድል የክስ ትያትር ባስቸኳይ እንዲቆም ለማድረግ የሚቻለውን ሁሉ እንዲያደርጉ ለኢትዮጵያ ህዝቦችና ለዓለም አቀፍ ማህበረ-ሰብ ጥሪያችንን ለማቅረብ እንገደዳለን።

ሌላው በዚህ ጉዳይ ዙርያ የሚነሳው ነጥብ "ቅንጅት የትግራይ ተወላጆችን ከማህበራዊ ህይወት አግልሉ የሚል አዋጅ አስነገረ" የሚለው የነመለስ አሉባልታ ነው። ቅንጅት ድምፁ የተነጠቀ ህዝብ መብቱን ለማስከበር መከተል የሚገባውን ሰላማዊ የትግል ስልት የዘረዘረበትን መግለጫ ተመልክተነዋል። ሰነዱ ውስጥ ግን የትግራይ ተወላጅን ከማህበራዊ ኑሮ አግልሉ የሚል ሐረግ የሰፈረበት ቦታ የለም። ነብሰ-ገዳይ ካድሬዎችና ከነሱ ጋር የሚተባበሩ ግለሰቦችን ስለ ማግለልና የኢህአዴግ የንግድ አውታሮች ለገበያ የሚያቀርቡት የፍጆታ ዕቃዎችን አስመልክቶ በየደረጃው መወሰድ ስለሚገባቸው ህዝባዊ አድማዎች ሰነዱ ውስጥ ሰፍሯል። እዛ ውስጥ የትግራይ ተወላጆችን ለይቶ የሚጠቅስ አንድም ዓረፍተ-ነገር የለም። እነዛ ጽንፈኛ የቅራኔ አጋፋሪዎች የሚነግሩንን እንደ እውነት ካልተቀበልነው በስተቀር ነብሰ ገዳይ የኢህአዴግ ካድሬዎችም ሆኑ ደጋፊ የጥቅም ተጋሪዎቻቸው የትግራይ ተወላጆች ብቻ አይደሉም። ለኢህአዴግ ያደገደገ ከሁሉም ብሔርና ብሔረ-ሰቦች አለበት። የህወሓት መሪዎችና አጋፋሪዎች ሊያሳምኑን እንደሚቃጡትም "ህወሓት ማለት የትግራይ ህዝብ ማለት ነው" የሚለው ዝባዝንኬን አንቀበልም። ህወሓትና የትግራይ ህዝብ የተለያዩ መሆናቸውን ለማስረገጥ ጽንፈኞችንም ሆነ የህወሓት መሪዎችን ለምስክርነት መጥራት አያስፈልገንም። እንዲያው በቁጥር ካየነው በዚህ የሽበራ ተግባር የተሰማራው አድርባይ ከሌላው ብሔርና ብሔረ-ሰቦች እንደሚበዛም አንጠራጠርም። ስለሆነም የኢህአዴግ የጥቅም ተካፋዮችና አስከባሪዎች እንደሚሉን ቅንጅት ከማህበራዊ ኑሮ እንዲገለሉ የሚለው የትግራይ ተወላጆችን ሳይሆን ባጠቃላይ ነበሰ ገዳዮችንና የኢህአዴግ የንግድ ኩባኒያዎችን ስለሆነ ዕቅዱ በተግባር ከዋለ ይበልጥ የሚጎዳው የሌላ ብሔር ብሔረ-ሰብ ህዝብና ኢህአዴግ ናቸው። ስለዚህ "ቅንጅት የትግራይ ተወላጆችን አግልሉ ብለዋል" ብሎ ከመጨነቅ እነ መለስና ካድሬዎቹ ከሚፈጽሙት ወንጀል ተቆጥበው የህዝብና ያገር ሉዓላዊነት እንዲቀበሉና እንዲያከብሩ መታገል ይበጃል።

ለመሆኑ እነዚህ ዛሬ ቅንጅት የትግራይ ተወላጆችን አግልሉ ብለዋል እያሉ የአዞ እምባ የሚያነቡት የህወሓት ካድሬዎች ኢህአዴግ የሽግግር መንግሥት ባቋቋመበት ወቅት ኢዲዩ የሆነ ወይም በኢዲዩነት የተጠረጠረ ዜጋ፣ ትግራይ ውስጥ ከማህበራዊ ህይወት እንዲገለል በህወሓት መሪዎችና ካድሬዎች ሲወስኑና በተግባርም የትግራይ አዛውንቶች ለህይወታቸው ሰግተው እግር አውጭኝ ወደ አዲስ አበባ ሲሸሹ የዛሬዎቹ ለትግራይ ህዝብ "መብት" ተቆርቋሪ ካድሬዎች የት ነበሩ? ወይስ ያው እንደ ተለመደው አንድ ወንጀል በህወሓት መሪዎች ከተፈጸመ ቅዱስ፣ በሌላ ከተደገመ ደግሞ እርኩስ ነው የሚለውን የድርጅቱን ሰንካላ ባህል ለመከተል? እዚህ ላይ ማንም ያርገው ማንም አንድ ወንጀል ከተፈጸመ ቦታም ሆነ ጊዜ ሊሽሩት አይችሉም። ቅንጅትም ቢሆን ካደረገው የህወሓት መሪዎች ቀድመው ስላደረጉት ነፃ ይሆናል ሊባል የሚቻልም አይደለም።

ት.ዴ.ትም ማንም ያርገው ማን የወንጀል ድርጊትን ሁሌም አውግዟል ለወደፊትም ያወግዛል። ለዚህ እምነቱም ጸንቶ እንደሚታገል ለጠላትም ለወዳጅም ግልጽ ማድረግ ይፈልጋል።

ስለ ኢህአዴግ መሪዎች ፖለቲካዊ ባሕሪ ይህንን ያህል ካልን ዘንዳ ወደ ሌላኛው አደገኛ ጽንፈኛ የጥላቻ ኃይል ባሕሪ እናምራ።

ይህ ጽንፈኛ የጥላቻ ኃይል በተለያዩ ጊዜያቶች ራሱን አደራጅቶ ለመውጣት ቢሞክርም አልሳካልህ ስላለው ዛሬ ከሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች ጋር በጥገኝነት ተቆራኝቶ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ኃይል ነው። ይህ ኃይል ለማህበራዊ ለውጥ የመታገል ተፈጥሮ ሊላበስ የሚችል ኃይል አይደለም። መላው ህዋሳቶቹ በጥላቻ የተበከሉ በመሆናቸው ስለ ማህበራዊ ለውጥ ለማሰብ የሚያስችል አቅምም የለውም። ሌላው ይቅርና ጨቋኝ አገዛዝንና ተጨቋኝ ህዝብን ለይቶ የማየት ችሎታም ሆነ ህልና የለውም። አሁን ለማስመሰል ከአንዱ ወይም ከሌላው ዴሞክራሲያዊ ወይም ሀገራዊ ኃይል ጋር በጥገኝነት ተቆራኝቶ ለመጓዝ መሞከሩ አቅም ከማጣት የሚመነጭ እንጂ ፖለቲካዊ አመለካከቱን ስለ ለወጠ አይደለም። ባሕሪው ከተጠጋበት ድርጅት ጋር ሊያስኬድው እንደማይችል ሲያውቅ ተለይቶ ይወጣል፤ ካልሆነም ይባረራል። ባንድ ወቅት ላይ ባንድ ወይም በሌላ መልኩ የጽንፈኞች ስብስብ ፈጥሮ መንቀሳቀስ እንደሚጀምር የሚያጠራጥር አይደለም። ይህ ኃይል ሀገራዊም ሆነ ህዝባዊ ራእይ ባይኖረውም የብዙ የዋህ ኢትዮጵያዊያን ጭንቅላትን በጥላቻ መርዝ ለመበረዝ በሚያደርገው እንቅስቃሴ የተወሰኑ ተከታዮች እያፈራ መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው። ዕድል ገጥሞት ራሱን ካደራጀ በያዘው የጥላቻ ጎዳና መራመዱ ስለማይቀር ላገር ህልውና አደጋ እንደሚሆን በወቅቱ መታወቅ አለበት። በይዘቱ ከኢህአዴግ አይለይም የምንለውም ይህ በታኝ የጥላቻ ባሕሪውን በመገንዘብ ነው።

ይህ በታኝ ጽንፈኛ የጥላቻ ኃይል ዛሬ የጥላቻ ጦሩን ያነጻጸረው በትግራይ ህዝብ ላይ ነው። ትግራይ የታሪካችን መሠረት ከመሆኑም በላይ የትግራይ ህዝብ እንደማነኛውም ኢትዮጵያዊ በሚፈለግበት ሁሉ ሀገራዊ ግዳጁን ሲወጣ የኖረ ህዝብ በመሆኑ እንደ ህዝብ መከበር ይኖርበታል። ባጠቃላይም እንደ ህዝብ የሚጠላ ህዝብ መኖር የለበትም። ይህ ጽንፈኛ የጥላቻ ኃይል ግን ይህንን ሓቅ የመገንዘብ አቅም የለውም። ዛሬ እነ አምባገነኑ መለስ ከትግራይ መጥተው ሥልጣን ላይ በመቀመጥ አገርን ሲከፋፍሉና ህዝብን ሲያበጣብጡ በማየት የትግራይን ህዝብ እንደ ተባባሪ ወንጀለኛ አድርጎ መፈረጅ አደገኛ ስሕተት ነው። ቢሆንም ይህ ጽንፍኛ የጥላቻ ኃይል ሥልጣን ተረክቦ እነ መለስ የሚያደርጉትን ራሱ ለማድረግ የቋመጠ ኃይል በመሆኑ ይህንን የማገናዘብ አቅም እንዲኖረው አይጠበቅም። የጥላቻው መጨረሻም የትግራይ ህዝብ ላይ የሚያቆም አይሆንም። ነገ የኦሮሞ ድርጅት ሥልጣን ቢይዝ የኦሮሞን ህዝብ፤ የዓፋር ድርጅት ሥልጣን ቢይዝ የዓፋርን ህዝብ፤.....ወዘተ. እንደጠላት ማየቱ የማይቀር ነው።

ይህ ጽንፈኛ የጥላቻ ኃይል በትግራይ ህዝብ ላይ ከፍትኛ የማጥላላት የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ከፍቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ከዚህም አልፎ የትግራይ ህዝብንና የፖለቲካ ድርጅትን ለይተው የሚያዩት የፖለቲካ ድርጅቶችን ይኮንናል የስም ማጥፋት ዘመቻም ይከፍትባቸዋል። ከጥላቻ ዘመቻዎቹ አንዳንዱን ለናሙና ያህል ማስቀመጡ ለግንዛቤ ይረዳል።

የትግራይ ህዝብ የኢትዮጵያ ካንሰር ስለ ሆነ ተቆርጦ ይጣል፤ ትግርኛ ተናጋሪውን ባጥር ከልለን በቦታው እንዲወሰን እናድርገው፤ ትግራይ በልማት ልትሰምጥ ነው፤ የትግራይ ህዝብ ያገዛዙ ተጠቃሚ ነው፤ የትግራይ ተወላጆች በሙሉ የኢህአዴግ ደጋፊዎች ናቸው፤ ከማለት አልፎ የትግራይ ህዝብ ኢትዮጵያዊ አይደለም፤ አገራችን ቅኝ ተገዥ ሆናለች እስከ ማለት መድረሱ በግልጽ የሚታይና የሚደመጥ ሀቅ ነው። በዚህም እነ መለስ አጥብቀው የሚፈልጉት የከፋፋይነት መሳርያ ሆኖ ለካድሬዎቻቸው ዱላ ከማቀበሉም በላይ በህዝቦች መካከል የማያባራ እሳት ሊጭር የሚችለውን ከኢህአዴግ መሪዎች ውጭ ማንንም የማይጠቅም ጥላቻ በህዝቦች ውስጥ በመርጨት ሥራ ተወጥሮ ይገኛል። ይህ ከነመለስ ካድሬዎች የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ባልተናነሰ መልኩ የሚያራምደው አደገኛ የጥላቻ ቅስቀሳ ወዴት እንደሚያመራ ለመገንዘብ የተለየ ብልህነት እንዲኖረን አያስፍልግም።

የዚህ ጽንፈኛ የጥላቻ ኃይል ሰለባ የሆኑት አንዳንድ ዋልጌዎች በቀጥታና በተዘዋዋሪ በትግራይ ተወላጆች ላይ የሚያደርሱት በደልና የሚፈጥሩት ጫና የንፁሑን የትግራይ ተወላጅ ሂሊና በመንካት ላይ ነው። አዲሰ አበባ ከተማ ውስጥ ሹሩባ ተሰርታ የምትወጣ ሴት የሚደርስባት

ማንጓጠጥ፣ በህዝባዊ ዓመጹ ወቅት በትግራይ ተወላጆች ንብረትና ህይወት ላይ ሆን ተብሎ ባንዳንድ ዋልጌዎች የደረሰው ከህዝባዊ ዓመጹ ዓላማና መንፈስ የራቀ ተግባር፣ አሁን በየድረ-ገጹ የምናነባቸውና ባንዳንድ ሬዲዮ ጣቢያዎች ሲተላለፉ የምንሰማቸው ዘለፋዎች፣...ወዘተ. ተደማምረው ህዝቡን የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ እንዲሆን አድርገውታል። የነመለስ ካድሬዎች የጥላቻ ሰበካም በፍርሃት በተዋጠው ህዝብ ውስጥ ለጊዜውም ቢሆን እየሰራ ነው። ኢህአዴግም እነዚህን ዋልጌዎችና ጽንፍኞች ለዋሉለት ውለታ በልቡ እንደሚያመሰግናቸው ጥርጥር የለውም። በዚህ ተግባራቸውም ኢህአዴግ ራሱ ሊያሰባስበው ያልቻለውን ህዝብ ስለ አሰባሰቡለት ሙሉ በልብ እንዲሉ በግልጽ አይናገረው እንጂ ማመስገኑ አይቀርም። አንዳንዶቹም ለዚህ ሥራ በራሱ በኢህአዴግ የተመለመሉ ሊሆኑ እንደሚችሉ መጠርጠሩ አይከፋም።

እንግዲህ ተጠቃልሎ ሲታይ እነዚህ ሁለቱ ከላይ የጠቀስናቸው ኃይሎች ጥላቻን በመዝራት እጅጉን ይመሳሰላሉ። ልዩነታቸው ጥላቻን ከማስፋፋት ባሕሪ ወይም ይዘት የሚመነጭ ሳይሆን ለየራሳቸው ካስቀመጡት የግብ ልዩነት ነው። ይህ ሁለቱ የጥላቻ ኃይሎች በየፊናቸው የሚያስተጋቡት የአጣሉኝ መርዝ በጊዜ ካልተመከተ ከፍተኛ ብሔራዊ አደጋ ሊያስከትል የሚችል መጥፎ አካሄድ ነው። የሚገርመው ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሻዓቢያ ሬዲዮና ተለቭዥንን በዚህ በኢትዮጵያዊያን መካከል ጥላቻ የመዝራት ዘመቻ ላይ ተሠማርተው መገኘታቸው ነው።

ስለሆነም አገር ወዳዶችና ዴሞክራሲያዊያን ኃይሎች ትኩረታቸው ሥልጣን በጨበጠው ዋናው የጥላቻ ኃይል ላይ ባነጣጠረበት ባሁኑ ወቅት ይህ አጥፊ ኃይል ራሱን አጠናክሮ በመውጣት ህዝባዊ ትግሉን እንዳይመታና እንዳይከፋፍል ከወዲሁ እንዲታገሉት ያስፈልጋል እንላለን።

ይህንን ሁሉን የጥላቻ ኃይሎች ባንድነት የመታገል ግባቸውን ባጭር ጊዜ እውን ለማድረግ እንዲችሉ ከተፈለገ ደግሞ ትግላቸውን ይበልጥ ማጠናከርና ማቀናጀት ይጠበቅባቸዋል። ይህ አካሄድን በጋራ የማዋደድ ጥያቄ ወቅታዊ ጥያቄ ነው ብለንም እናምናለን። ይህንን ወቅታዊ ጥያቄ በጋራ ለመጋፈጥ ወቅቱ የሚጠይቀውን የጋራ መስዋእትነት በጋራ ለመክፈል ዝግጁ ለመሆን ካልበቃን፣ አገራችንን ከተደቀነባት የመበታተን አደጋ ለማዳን የማንችልበት ሁኔታ ይከሠታል ብለን እንሰጋለን።

ያለንበት ወቅት የአገራችንን ህልውና ዘላቂነት ባለው መልኩ እንዲቀጥል የማስቻል ጥያቄ ተገቢ መልስ ማግኘት ያለበት ወቅት መሆኑ ሁሉም አገር ወዳዶችና ዴሞክራሲያዊያን ኃይሎች በወጉ ሊገነዘቡት ይገባል። ላገራችን ዘላቂ መፍትሔ በማሻት ከውድቀት ታድገን እውነተኛ ትንሳኤዋን ለማብሰር የምንሻ ዜጎች በጋራ እንድንሰራ የሚያስገድደን ወቅት ደርሷል። ለዚህም ነው ዛሬ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊያን ኃይሎችና አገር ወዳዶች እያንዳንዳቸው በፖለቲካ ፕሮግራሞቻቸውና በሌሎች ልዩነቶች ዙርያ የሚነሱ አጀንዳዎችን በይደር ይዘው፣ የአገራቸውን ህልውና ለማስከበር ከምን ጊዜም በላይ አብረው ለመቆም የሚገደዱበት መድረክ ላይ ነን የምንለው። አገራችን አስፈሪ በሆነ የመበታተን አደጋ ውስጥ ስለምትገኝ የጋራ የትግል ስልትን መቀየስና መከተል በይደር የምናቆይበት ምቾት ላይ እንደሌለን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ለገንቢ ዓላማ ፈጥነን በጋራ መቆም ካልቻልን መድረኩን ጥላቻ ማስፋትን ሰንቀው በገሀድና በስዉር ለሚንቀሳቀሱ ቡድኖች መተው ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያሻል። እነዚህ አፍራሽ ፀረ-ህዝብ ኃይሎች መድረኩን ከተቆጣጠሩት ደግሞ የምንመኘው ያገራችን ህልውናና የህዝቦቻችን ሰላማዊና የተረጋጋ ኑሮ ላይ ሊከተል የሚችል አደጋ በቀላሉ የሚገመት ካለመሆኑም በላይ የርስ በርስ ጦርነትን ያስከትላል። ዛሬ አገሪቱን በመግዛት ላይ ያለው አምባገነን ቡድንም የማይቀረው የመውደቅያው ቀን ሲደርስ ለሥልጣኑ ማራዘምያ ሲጠቀምበት የቆየውን የከፋፍለህ ግዛ ስልቱን በበለጠ ስፋትና ጥልቀት ተግባራዊ ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማይል ይታወቃል። ስለሆነም አገሪቱ ብትንትኗ እንድትወጣ የነደፈውን ዕቅድ ተግባራዊ ያደርጋል። በይዘትና በተግባር ከእርሱ የማይለዩት ጽንፈኞችም ከራሳቸው የጥላቻ ባሕሪ በተጨማሪ ኢህአዴግ ባዘጋጀላቸው ወጠመድ ውስጥ በቀላሉ ስለሚገቡ፣ አገር የማፍረስ ሴራው አካል ሆነው እንደሚሰለፉ ከወዲሁ መታወቅ አለበት።

አገር ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ኢህአዴግን የሚጠሉበት ዋናው መሠረታዊ ምክንያት ድርጅቱ ላገርና ህዝብ ካለው አጀንዳ ጋር የተገናኘ እንጂ ኢህአዴግ ስለሆነ አይደለም። በዚህም

ለኢህአዴግ ያላቸው ጥላቻ ህዝብን ከህዝብ ጋር ለማናከስ ከሚራወጡት ኃይሎች ጥላቻ ፍጹም የተለየ ነው። አገር ወዳዶችና ዴሞክራሲያዊያን ኃይሎች ኢህአዴግን የሚጠሉት ላገራችንና ለህዝቦቿዋ መሠረታዊ ማህበራዊ ለውጥ የማምጣት ራእይ ስላላቸው ነው። የኢህአዴግ መሪዎች ግን ሀገራዊም ሆነ ህዝባዊ አጀንዳም ራእይም የላቸውም። የሚያጣላቸው ይኸው የራእይ ልዩነት ነው። ህዝብንና የፖለቲካ ኃይልን ለመለየት ከማይችሉና እንደ ኢህአዴግ ህዝብን ከህዝብ ጋር በማናከስ ለማትረፍ ከሚራወጡ ኃይሎች ጋርም የሚለዩት በዚህ ነው። የጥላቻ ኃይሎች በራእይ ከኢህአዴግ አይለዩም። ምኞታቸው ኢህአዴግ የሚያደርገውን በተራቸው ማድረግ ነው። በዚህ ህልማቸውና ምኞታቸውም ካገር ወዳዶችና የዴሞክራሲያዊያን ኃይሎች ይለያሉ።

ኢህአዴግ የማንንም ህዝብ ድጋፍ የሌለው የስግብግብ አምባገነኖች ስብስብ ሆኖ እያለ፤ ህዝብ ተባብሮ እንዳይነሳበት የጽንፈኞቹን ከፋፋይ የጥላቻ ዘመቻ በመጠቀም ሥልጣን ላይ ተንጠልጥሎ ሊሰነብት ችሏል። በዚህም የተጎዳው አገራችንና መላው ህዝባችን መሆኑም ግልጽ ነው። ጽንፈኞቹ በተያያዙት ከፋፋይ የጥላቻ ዘመቻ ቢቀጥሉ ኢህአዴግ የተመኘው ክፍፍል በህዝቦች መካከል እየሰፋ ስለሚሄድ ሥልጣን ላይ መሰንበቱና በቀላሉ የማያባራ ሀገርን የሚያናጋ ግጭት ሊቀሰቅስ እንደሚችል መገንዘብም ያስፈልጋል። በመሆኑም ዴሞክራሲያዊያንና ሀገር ወዳድ ኃይሎች ይህንን አደጋ በመገንዘብ ሰፊውን ህዝብ በአንድ ሀገራዊ ራእይ መፈክር ሥር አሰባስበው በማደራጀት የአምባገነኖችና የጽንፈኞችን አደገኛ አካሄድ በማክሸፍ ህዝባዊ ድል እንዲቀዳጁ ከተፈለገ ከምን ጊዜም በበለጠ መተባበር ይጠበቅባቸዋል።

ድል በህዝባዊ ትግል!!!
ውድቀት ለከፋፋዮችና ለጥላቻ አስፋፊዎች!!!

ት.ዴ.ት ሚያዝያ 1998 ዓ.ም